## ምስጢረ ተክሊል

**ጥያቄ፤- ሕጋዊ ጋብቻ የተመሠረተዉ በማን ፈቃድና በማን ቡራኬ ነዉ?**

ሕጋዊ ጋብቻ የተመሠረተዉ በእግዚአብሔር ቡራኬ ነዉ። «ሰው (አዳም) ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለምና የምትረዳዉ ጓደኛ እንፍጠርለት» ብሎ እግዚአብሔር ሔዋንን ከአዳም አካል ፈጠራት (ዘፍ.2፣ 18)።

አዳምም ከአካሉ የተፈጠረችዉን ሰዉ አይቶ እንዲህ አለ «ይህች አጥንት ከአጥንቴ፣ ይህች ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል (ተብላ ትጠራ)»(ዘፍ.2፣23-25)።

«እግዚአብሔር አምላክ ሰዉን በመልኩ ፈጠረ፣ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸዉ፣ ከዚያም እንዲህ ብሎ ባረካቸዉ፣ ብዙ ተባዙም፣ ምድርንም ሙሉዋት፣ ግዟትም (አስተዳድሯትም)፣ የባህር ዓሦችና የሰማይ ወፎችን፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ግዟቸዉ» (ዘፍ.1፣26-31)

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ ተገልጦ ወንጌል መንግሥትን እየሰበከ በዓለም ላይ በሚዘዋወርበት ወቅት ጋብቻ እጅግ የተቀደሰ መሆኑን በምስጢረ ጋብቻ እግዚአብሔር አንድ አካል ያደረጋቸዉን ባልና ሚስት ሰዉ ሊለያያቸዉ እንደማይገባ አረጋግጧል (ማቴ.19፣3-7፤ ማር. 10፣2-9)። በተጨማሪም ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕገ ቤተክርስቲያን የሚፈጸመዉ ጋብቻ ቅዱስ መሆኑን ለማረጋገጥ በሕግ የተጋቡትን ለመባረክ በቃና ዘገሊላ ከተማ በተደረገዉ ሠርግ ላይ ተገኝቷል (ዮሐ. 2፣1-11)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቤተክርስቲያን ሥርዓት ጋብቻቸውን የፈጸሙ ተጋቢዎች ጋብቻቸው የተቀደሰ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ፣ በተቀደሰ (በተባረከ) ጋብቻ አንድ የሆኑ ተጋቢዎች፣ በመንፈሳዊ ሕይወት የተሳሰሩ አንድ አካል መሆናቸዉን ገልጿል፤ «የገዛ ሚስቱን የወደደ ራሱን ይወዳል፣ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና» ሲል ባልና ሚስት አንድ አካል መሆናቸዉን መስክሯል (ኤፌ. 5፣21-33)። በሌላ መልእክቱም፣ በሕገ ቤተክርስቲያን የተፈጸመ ጋብቻ ንጹሕና ክቡር መሆኑን አስተምሯል (ዕብ. 12፤1-6)። ስለዚህ በሥርዓተ ተክሊል ማለት በቤተክርስቲያን ሥርዓት የሚፈጸም ጋብቻ ሁሉ በእግዚአብሔር ስም የተባረከ በመሆኑ፣ ሊፈረስ አይገባውም፤ «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን (ያጣመረውን) ሰው አይለየውም» ተብሎ የተሰጠውን አምላካዊ ትእዛዝ ምን ጊዜም መከበር አለበት (ማር.10፣1-9)።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ላይ ተገኝቶ፤ በሕግ የተጋቡትን ወጣቶች እንደ ባረካቸው የታወቀ ነው (ዮሐ. 2፤1-11)። በዚሁ መሠረት በጌታችን ተከታዮች ቡራኬ የተፈጸመ ጋብቻ መፍረስ እንደማይገባው ራሱ ጌታችን በጋብቻ አንድ የሆኑ ሴትና ወንድ ፣ «አንድ አካል ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም» ሲል አስተምሯል (ማቴ. 19፣6)።

ባልና ሚስት መፋታት የማይገባቸው መሆኑን አስመልክቶ የኦሪቱን ሕግ በማስተካከል ጌታችን ያዘዘው በድጋሚ እንጠቅሳለን «ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት እንደተባለ (በኦሪቱ ተብሏል)፤ እኔ ግን እላችኋለው ያለ ዝሙት ምክኒያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል» (ማቴ.5፣31-33)።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረው ማንም ሰው ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ቢፈታ እስዋን አመንዝራ ወይም ዝሙት አዳሪ እንድትሆን ያደርጋታልና ሰዉየው በደለኛ ይሆናል። ሴቲቱም ባልዋን ያለ ዝሙት ምክንያት ብትፈታውና ሰውየዉም አመንዝራ ወይም ዘማዊ ቢሆን፣ ለዚህ ኃጢአት ያበቃችው ሚስቱ ኃጢአተኛ ናት።

ስለዚህ ባልና ሚስት ከኃጢአትና ከበደል ይድኑ ዘንድ በሕገ ቤተክርስቲያን አማካይነት የገቡት
ን የጋብቻ ቃል ኪዳን እስከ ዕለተ ሞታቸዉ ድረስ ጠብቀው መኖር ይገባቸዋል። በጋብቻቸው
ጊዜ በእግዚአብሔር ስም ቤተክርስቲያን የገቡትን ቃል ኪዳን ማፍረስ ዐቢይ ኃጢአትና ትልቅ
በደል መሆኑን ምን ጊዜም መርሳት አይገባቸውም።

## እጅግ ጠቃሚ ምክር

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ በታች የሰጠውን ምክርና መመሪያ መከተል ይገባል፤ «ባሎች
ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ። በውኃ ጥምቀትና
በቃሉ ያነጻት ዘንድና ይቀድሳትም ዘንድ ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ። ነውርና እንከን ጉ
ድፍ ሳይኖርባት ንጽሕትና ቅድስት ትሆን ዘንድ ለራሱ አደረጋት። እንደዚሁም ባሎች ሚስቶቻ
ቸውን እንደ ራሳቸው አድርገው ሊወዱ ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤
የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና። የአካሉ ክፍሎች ስለሆንን ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን እን
ደሚመግብ እናንተም ሚስቶቻችሁን መግቡ ተንከባከቡም። ስለዚህ ሰው (ባል) አባቱንና እናቱን
ይተዋል ሚስቱንም ይከተላል ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ። ይህ ምስጢር ታላቅ ነው። እኔ
ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እላለሁ። ነገር ግ እናንተ እያንዳንዳችሁ ሚስቶ
ቻችሁን እንደ ራሳችሁ አድርጋችሁ ውደዱ፤ ሚስት ባሏን ታክብረው» (ኤፌ. 5፣26-33)።

ከትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት 1991 አቡነ ገብርኤል ከጻፉት የተወሰደ።